DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## የበልግ (fall) 2022 የፓኖራማ (PANORAMA) የተማሪ እና የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት ማስታወቂያ እና መልቀቂያ (WITHDRAWAL) ደብዳቤ

October 3, 2022

ውድ ወላጆች እና አሳዳጊዎች እና አዋቂ (Adult) ተማሪዎች፡

**የበልግ (Fall) 2022 የፓኖራማ (Panorama) የተማሪ የዳሰሳ ጥናት፣** ማክሰኞ፣ ኦክቶበር (October) 17 እንደሚጀመር ስናስታውቅ ደስታ ይሰማናል!

> በፀደይ (spring) 2022 እና ከዚያ ቀደም-ብሎ ተደርጎ የነበረውን በዲስትሪክ-ደረጃ ያለውን፣ የቤተሰብ እና የተማሪ የዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን፤ በbit.ly/dcpsresults ይመልከቱ።
>
> በፀደይ (spring) የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ላይ ጎልተው የሚታዩ ነገሮችን በhttps://dcps.dc.gov/surveys ላይ ያንብቡ።

DCPS እና የትምህርት ቤት አስተዳደሮች፣ ተማሪዎች ስለትምህርት ቤት ተሞክሮዎቻቸው እና የማህበራዊ እና ስሜታዊ መማር ምን እንደሚያስቡ በተሻለ-ሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለመርዳት፤ በ3ተኛ እና ከዚያ በላይ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ለዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የፓኖራማ የተማሪ የዳሰሳ ጥናት (Panorama Student Survey)፤ ስለ ማህበራዊ ስሜታዊ መማር (social emotional learning)፣ ተማሪዎች የዳሰሳ ጥናትን፤ በዓመት-ሁለት ጊዜ፣ እንዲያጠናቅቁ እንጠይቃለን። **በዚህ በልግ (fall)፣ የተማሪ የዳሰሳ ጥናት፣ ከኦክቶበር (October) 17 እስከ ህዳር (November) 4** ድረስ ክፍት ይሆናል። እያንዳንዱ ተማሪ፣ የተማሪ የመታወቂያ (ID) ቁጥራቸውን ተጠቅመው በመግባት፣ በhttps://surveys.panoramaed.com/dcps/login ላይ የዳሰሳ ጥናቱን መሙላት ይችላሉ። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች፣ በኦንላይን ክፍለጊዜዎች ወቅት ወይም በወረቀት ላይ፣ የዳሰሳ ጥናቱን ያካሂዳሉ።

ልጅዎ እንዲካፈል ካልፈለጉ፣ **ልጅዎ ከዳሰሳ ጥናቱን እንዳይሞላ (opt out) ሊያደርጉት ይችላሉ።** ዕድሜያችሁ 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆናችሁ ተማሪዎች ከሆናችሁ፣ ከዳሰሳ ጥናቱ እራሳችሁን ለማስወጣት (opt out ልታደርጉ) ትችላላችሁ። የመውጫው፣ (opt out የማድረጊያው) የመጨረሻ ቀን ኦክቶበር (October) 21 ቀን ነው። የዳሰሳ ጥናቱ ከተጀመረ በኋላ ከወጡ (opt out ካደረጉ)፤ ልጅዎ በክፍል

> በዚህ በልግ (fall)፣ ልጅዎ የፓኖራማ (Panorama) የተማሪ የዳሰሳ ጥናትን እንዲሞላ ካልፈለጉ፤ ወይም፣ የ18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ የሆናችሁ ተማሪዎች ከሆናችሁ እና የዳሰሳ ጥናቱን መውሰድ ካልፈለጋችሁ፣ እስከ **ኦክቶበር (October) 21 ቀን 2022**ድረስ ይህን ቅጽ ሙሉ:
>
> የበልግ (Fall) 2022 የፓናሮማ (Panorama) የተማሪ መውጫ (Opt-Out ማድረጊያ)።
>
> *ቅጹን ለመሙላት፤ የልጅዎ የተማሪ የመታወቂያ ቁጥር (ID) ያስፈልግዎታል።*

ውስጥ እንዲሞላ ይጠየቅ ይሆናል፣ ነገር ግን የሰጡት ምላሽ አይቆጠርም።

**ይህ የዳሰሳ ጥናት በፍቃደኝነት የሚደረግ እና ሚስጢራዊነትን የጠበቀ ነው።** ልጅዎ እንዲካፈል አያስፈልግም፤ ነገር ግን አስተያየቱ (feedback) በጣም ዋጋ ይኖረዋል። የዳሰሳ ጥናቱ፣ የልጅዎን እውነተኛ የሆነ ተሞክሮን እና አስተያየቶች ብቻ ይጠይቃል። የልጅዎ የውጤት ደረጃው፣ በሰጠው/ችው ምላሾች ምክንያት ተጽዕኖ አይኖርበትም። ሕጉ እስከሚፈቅደው ድረስ፣ የልጅዎ ግላዊ መረጃ የተጠበቀ ይሆናል። በሪፖርቶቹ ላይ፣ የልጅዎ ስም በጭራሽ በጥቅም ላይ አይውልም። በቀደሙት ዓመታት እንደተደረገው፣ ከ6-12ኛ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን፣ ስለ ፆታቸው እና ወሲባዊ ማንነት፤ የዳሰሳ ጥናቱ ይጠይቃል። እነዚህ ጥያቄዎች፣ ፆታን የቀየረ (Transgender) እና ፆታ-ያለማረጋገጥ (Gender-Nonconforming) የፖሊሲ መመሪያችንን በተከተለ ሁኔታ፤ ዲስትሪክቱ ለሁሉም ተማሪዎች፣ እክል የሆነ እንክብካቤን ለማበረታታት ይረዳዋል። ሙሉ በሙሉ በፍቃደኝነት የሚመለስ፣ እና ለመመለስ ምቹ ስሜት የማይሰማቸው ተማሪዎች፣ ጥያቄዎቹን ሊዘሏቸው ይችላሉ።

**የልጅዎን ፍላጎቶች በበለጠ ለመረዳት፣ ትምህርት ቤቶች የዳሰሳ ጥናት ውጤቶቹን ይጠቀማሉ።** የDCPS አንዱ አካል የሆነው፣ ባለ በርካታ ዘርፍ የእርዳታዎች ዘዴ ማነሳሻነት (Multi-Tiered System of Support initiative (MTSS @ DCPS)፤ አስተማሪዎች እና ሠራተኞች፣ የተማሪዎችን የፓኖራማ ውጤቶችን ጎን-ለጎን - ከቀለም ትምህርት፣ በትምህርት ገበታ መገኘት (attendance)፣ እና የባሕሪያዊ የመረጃ ስብስብ (data) ጋር አድርጎ ለመመልከት የሚያስችላቸውን፤ የፓኖራማ የተማሪ ስኬት ፖርታል (Panorama Student Success portal)ን ይጠቀማል። የፓኖራማ የተማሪ ስኬት (Panorama Student Success)ን በመጠቀም፤ አስተማሪዎች የልጅዎን አማካኝ የውጤት-ደረጃዎች (scores) - በዳሰሳ ጥናቱ ላይ፣ በተለያየ የSEL ርዕሶች ላይ መመልከት ይችላሉ። ተማሪው የግል ጥያቄዎችን እንዴት እንደመለሰ ማየት የማይችሉ እና ማንኛውም ከተማሪው የእርካታ (Satisfaction) ጥያቄዎች ወይም በፆታ እና በወሲባዊ ማንነት ጥያቄዎች ላይ ማንኛውንም መረጃ መመልከት አይችሉም። መድረኩ (The platform) ጥበቃው የተረጋገጠ (secure) እና በአስተማሪዎች ወይም በተማሪው ትምህርት ቤት ውስጥ ባሉ ሠራተኞች ብቻ ሊገኝ የሚችል ነው።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

የፓኖራማ የተማሪ የዳሰሳ ጥናት (Panorama Student Survey) እና የፓኖራማ የተማሪ ስኬት መድረክ (Panorama Student Success platform)፤ በDCPS ስራ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ክፍሎች ናቸው። ስለ ፓኖራማ የተማሪ የዳሰሳ ጥናት (Panorama Student Survey) እና ስለ ፓኖራማ የተማሪ ስኬት መድረክ (Panorama Student Success platform) ማንኛውም ጥያቄዎች ካለዎት፣ ወይም ተማሪዎቹ የሚያገኟቸው የዳሰሳ ጥናት ጥያቄዎችን ለማየት ከፈለጉ፤ እባክዎ በhttps://dcps.dc.gov/surveys ይጎብኙ።

ከሰላምታ ጋር፣
የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች